# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 7 ቁጥር 4 ሚያዝያ 21 ቀን 2012 ዓ.ም.


## <u>ሜይ ዴይ ስንል</u>

*(የሜይ ዴይ ሰማዕታት 43ኛ ዓመት እና የ«ያ ትውልድ ተቋም» ድረ ገጽ 8ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

ዓለማችን ዛሬ እጅግ አሳሳቢ ወረርሽኝ ላይ ትገኛለች። በቅድሚያ በዓለም ደረጃ ለተከሰተው ኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሕይወታችሁን ላጣችሁ ሁሉ የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እንገልጻለን። በበሽታው ለተጠቃችሁ ምህረትን ይላክላችሁ። በስጋትና በጸሎት በየቤቱ ለተቀመጥነው የዓለም መድሐኒት መድሃኔዓለም ምህረቱን ይስጠን። የቤት እሥረኛ እንሆን ዘንድ፣ ሰለጠንን፣ ሃብት ኖረን ከፈጣሪያችን ቁጥጥር ውጭ ባዶ መሆናችንን የአሳየን አምላክ እስከ በደላችንና አጢያታችን ይቅር ብሎ ምህረቱን ያወርድልን ዘንድ መሃረነ ክርስቶስ እንላለን፣ በእንተ እግዚተነ ማርያም መሃረነ ክርስቶስ እንበል 12 አሜን!!! ኢድ ሙባረክ!!!

ለኢትዮጵያ በጎ ዓላማ አንግበው የተነሱ ልጆቿ፣ ማንነታቸውን ለሀገራቸው፣ ለሕዝባቸው የሰጡ ወጣቶቿ፣ ቅድሚያ ለአርሶ አደሩና ለላብ አደሩ ብሶት ፋና ወጊ የሆኑ አለኝታዎቿ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. የዛሬ 43 ዓመት ዓለም አቀፍ የሠራተኞችን ቀን ክብረበዓል አስመልክቶ ድምጻቸውን በየአካባቢው ለማሰማት በየሠፈሩ ለሰላማዊ ሰልፍ ወጡ።

“ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አሁኑኑ”፣ “የዴሞክራሲያ መብት ያለገደብ”፣ መሪ መፈክራቸው አድርገው ለታገሉለት ሕዝብ ሜይ ዴይ 1968 ዓ.ም.ን አድምቀውና አሸብርቀው የትግል ሜዳ እንዳደረጉት። በዓመቱ ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. ን ለላብ አደሩ ያላቸውን ቃል ኪዳን ሊያድሱ የዛሬ 43 ዓመት ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ተሰለፉ “ኢሕአፓ ፓርቲያችን ነው” ድምጻቸው በፋሺስቶች ጥይት ተዋጠ። ይህ የላብ አደሩን ቀን ለማክበር ከየአካባቢው የተንቀሳቀሰ የታዳጊና የወጣቶች ሰላማዊ ሰልፍ ሲጀመርና የፋሺስት ጥይት ሲርከፈከፍ እኩል ሆነ። አድፍጦና ተዘጋጅቶ ይጠባበቅ የነበረ የፋሺስት ክላሽና ቢ አር ሰልፉን የጦር አውድማ፣ የእልቂት ቀን፣ የደም ቀን አደረገው። በርካታ ወጣቶች በፋሽስቶች ጥይት በየአስፏልቱና በየጉራንጉሩ ተደፉ፣ አዲስ አበባና ሌሎች የክፍለሀገር ከተሞች ሳይቀሩ በወጣቶች ደም ታጠቡ። ፋሽስት መንግሥቱ ኃይለማርያም ሚያዝያ 6 ቀን 1969 ዓ.ም. “የኢሕአፓን ደም እናፈሰዋለን” ብሎ መሬት የከሰከሰውን በቀይ ቀለም የተሞላ ጠርሙስ ድንፋታ ተግባራዊ አደረገው። በእለቱ ከሁለት ሺህ ወጣቶች በላይ በአዲስ አበባ ብቻ በደርግ ጥይት ተለቀሙ። ከሰልፉ አምልጠው በየቤታቸውና በየጉራንጉሩ የተሸሸጉ ለሊቱን እየተለቀሙ ተረሸኑ።

በሁለት ዓመት ተኩል ሥልጣኑ ገዳይ ሁኖ ገዳይ ያበቀለው መንግሥቱ ኃ/ማርያም ደርግና አጃቢ ባንዳዎች የኢሕአፓን እንቅስቃሴ ለመደምሰስ ከአላቸው እቅድ በየጊዜው አሰሳና ግድያ እራሱን

እያሳደገ ለሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. አሰቃቂ ፍጅት አበቃቸው። በርካታ ቤተሰቦች በሀዘን ተዋጡ፣ ልቅሶና ቀብር በተከለከለበት ፍጅት የእናቶች እየዬ መሪር ሆነ። ሲጀመርም ከሳሽ፣ ዳኛ፣ ፍርድ ሰጪ፣ ገዳይ፣ ቀባሪ ሆኖ የተፈጠረው ደርግ በየአካባቢው የረሸናቸውንም በጅምላ ቀበራቸው። በኢትዮጵያዊ ባህላችን ከፋሽስት ጣልያን ቀጥሎ ሞትን ያራከሰ፣ የቀብር ሥነ ሥርዓትን ያጠፋ፣ በገደላቸው ብቻ ሳይሆን የሕብረተሰቡን ባህላዊ እሴት ያራከሰ ታሪክ ሊዘነጋው የማይገባ ጨካኝና አረመኔ አገዛዝ ቢኖር ደርግ ነው።

የየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት ግብታዊ መሆንና የተዘጋጀና የተደራጀ ሕዝባዊ ኃይል ባለመኖሩ የሠራዊቱ ኃይል ከሕዝቡ ጋር በመደባለቅ እንቅስቃሴው እንዳይከሽፍ አጋር ከመሆን አልፎ መሪ ሊሆን መከጀሉ ሀገሪቷን ለከፋ ውድቀት ዳርጓታል። የደርግን አገዛዝ ከጅምሩም የተቃወሙትና ለጥያቄ ያቀረቡት ተራማጅ ኃይሎች አካሄዱንና ዝንባሌውን በመረዳት ነበር። ኢሕአፓ ኖረ አልኖረ የደርግ አገዛዝ አረመኔነቱ በዚያ ብቻ አላበቃም። “መንግሥቱ ለዓመሉ ደም ይልሳል” ነውና እንጂ እውን እስቲ የኮሎኔል አጥናፉ አባተ መገደል እውን የመንግሥቱ ኃይለማርያምን የጭካኔ ጥልቀቱን፣ የሥልጣን ወዳድነቱን አያሳይምን? ደም ሱስ የሆነበት ፋሽስት መንግሥቱ በስተመጨረሻ በ1981 ግንቦት ወር መፈንቅለ መንግሥትን አስታኮ የረሸናቸው ከፍተኛ የጦር መኮንኖች እውን ሲገል ኖሮ ገድሎ የፈረጠጠ ቢያሰኘው ተግባሩ አይደለምን? ገና ከጅምሩ ከሕግ በላይ ሆኖ የረሸናቸው 54 የቀድሞ የዓፄ ኃይለሥላሴ ባለስልጣናትና የጄነራል አማን አንዶምና ሌሎች እርሸና የደርግን አካሄድ ከጥያቄ አስገብቶ ጥያቄ ቢያስነሳ አግባብ አልነበረምን? “ምሩን፣ ሊቀ መንበር ሁኑልን” እያሉ ከደህና ቤታቸው ተጠርተው የተረሸኑት ብርጋዴር ጀነራል አማን አንዶምና ብርጋዴር ጀነራል ተፈሪ ባንቴ እውን አዕምሮ ላለው ስለ ደርግ ተራማጅነት ሊከራከር ይችላልን? የጭካኔው ደረጃ ከተገዳዮቹ ተሻግሮ ቤተሰቦቻቸውን ማሰቃየትና መውደቂያ ማሳጣት እውን ደርግ ገና ያልተነገረለት “የሰው አውሬ” ቢባል ያስደንቃልን?

ዛሬ ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. እርሸና ስናስታውስ ይህን ሁሉ የምናነሳው ጭፍጨፋው የእርስ በእርስ መገዳደል ውጤት ሳይሆን የአንድ አምባገነን ቡድንና መሪ ብቻ ሳይሆን የፋሽስት አገዛዝ ተግባርና ድርጊት ውጤት መሆኑን ለማስረገጥ ነው። ሜይ ዴይ 1969ን ስንዘክር የተገዳደለ ትውልድ ሳይሆን የተገደለ ትውልድ፣ በጅምላ የተረሸነ ትውልድ ቀን እንደነበር ለመመስከር ነው። ወደ ቀይ ሽብር አንሂድና በዚህ ዕለት ከአንድ ቤት የተረሸኑት አራት ታዳጊ ወጣቶች፣ ከየቤቱ እየተለቀሙ የተረሸኑት ወጣቶች የደርግን ገዳይነት መስካሪ እንጂ የያ ትውልድን ገዳይነት አንጸባራቂ ሊሆን ከቶም አይገባውም።

በጊዜው የነበርን የያ ትውልድ አካላት ልንረዳ የሚገባን ኢሕአፓ የሕዝብን ጥያቄ ይዞ ተነሳ እንጂ ሌላ የፈጠረው ተአምር የለም። “መሬት ለአራሹ” ቢታወጅ ኢሕአፓ አዋጁን ድጋፍ ሰጥቶ አፈጻጸሙ ላይ ያነሳቸው ጥያቄዎች ውሎ ሲያድር ትክክለኛነቱን አስገነዘቡ እንጂ ለውንጀላ አይዳርገውም። “መሬት ለአራሹን” አዋጅ ተቀብሎ ከደርግ ጎን ተሰልፎ ሕዝብን ማታለል ነበረበት ካልተባለ በቀር። “ህድገት በኅብረት የውቀትና የሥራ ዘመቻ” ሲታወጅና ተግባራዊ ሲሆን “ከፈረሱ በፊት ጋሪው” ሲል ድምጹን ያሰማው ቅድሚያ የመሬት አዋጁ ተግባራዊ መሆን ስለሚገባው ነበር። በተጨማሪም በተለይ በደቡቡ የሀገራችን ክፍል የታጠቁት ባላባቶችና መሳፍንት ትጥቃቸውን እንደያዙ ወጣት ተማሪዎችን ማዝመት ማስፈጀት መሆኑን ሲጠቁም ትንቢት አልነበረም። ሌላም “የቶሎ ቶሎ ቤት. . .” እንደሚባለው ጥናት ተደርጎበት አስፈላጊው መሰናዶ ሳይደረግ ከተሜ እንቅስቃሴ ፋታ ለማግኘት ሲባል የደርግና ከባቢ ምሁራን ውጥን ተማሪዎቹን ለአደጋ ያጋልጣል የተባለውን ጩኸት ውሎ

ሳያድር በተለያዩ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሕይወታቸውን ያጡ ያልተነገረላቸው ወጣቶች ማጎደር ዛሬም ጊዜን ይጠብቃል።

1967 እና 1968 ዓ.ም. ደርግ ገና ከጅምሩ የመናገር፣ መሰብሰብ፣ መደራጀት በጥቅሉ የዴሞክራሲያ መብት አፍኖ ለመግዛት በ"ኢትዮጵያ ትቅደም" ስም ካስጠነቀቀ በኋላ የነበሩ የአገዛዝ ሂደቶች ከደርግ ስብስብነት ወደ አንድ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነናዊ ሥርዓት ሀገሪቷ እየተጓዘች እንደነበር ጠቋሚ ነበር። ትግሉ ለሀገርና ለሕዝብ ነውና ቀጠለ። ኢሕአፓ የሕዝብ ድጋፍ ያገኘው፤ ያነገበውና የተሸከመው የሕዝብን ብሶት ስለነበር ብቻ ነው። ኢሕአፓ ለምን ሙሉ 1968ን ደምቆ ታየ? ቢባል መልሱ የትግል ውጤት ነው። ኢሕአፓ እንደ መንግሥት ባጀት ተመድቦለት፣ እንደ መንግሥት ሎጂስቲክ ተሟልቶለት፣ እንደ መንግሥት የመገናኛ አውታሮች ተሟልተውለት፣ ሌላም ሌላ የትግል አባወራ የሆነ አልነበረም። ኢሕአፓ ኃይልና መከታ ክንዱ ልጁ የኢትዮጵያ ሕዝብና ወጣቱ ነበር። ለዚህ ደግሞ ደርግና ስብስቦቹን በአንድ ዓመት እድሜው ማንነቱን ያሳያቸው በ14ቱ ክፍለሀገራት ዘር፣ ሃይማኖት፣ ጾታና ዕድሜ ሳይለይ በኢትዮጵያዊነት ጥላ በማደራጀቱ ነበር። ሙያና ሥራ ሳይገድበው ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ሠራተኞች፣ ወታደሮች፣ ዴሞክራት ኃይሎች እያለ በየፈርጁ ማደራጀቱና ማታገሉ ለደርግና ለከባቢ ምሁራን እራስ ምታት መሆኑ አይካድም። ይህም ሆኖ ኢሕአፓ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም" ሲል በወቅቱ የነበሩትን የፖለቲካ ኃይሎች፣ የብዙሃን ድርጅቶች፣ የሃይማኖት አባቶችን ጨምሮ በሥልጣን ላይ ያለውንም ወታደራዊ መንግሥት አካቶ እንደነበር ያልሞተችው "ዴምክራሲያ" ዛሬም ታስነብበናለች። እና እውን እንነጋገር ከተባለ ከአንድ ፈላጭ ቆራጭ የደርግ መኮንኖች አገዛዝና ደርግን ተገን አድርገው ስልጣን ሊቆናጠጡ ከቋመጡ አድርባይ ምሁራን ጥርቅም ይልቅ የጋራ አመራር መኖሩ እውን ምኑላይ ነው ጉዳቱ? አዎ! የማይካድ ጉዳይ ኢሕአፓ እጅግ ትልቅ ሀብት አካብቷል፣ እጅግ ግዙፍ መሣሪያ ታጥቋል፣ እጅግ ጠንካራ ቤት አለው. . . ሕዝብ፦ ላብ አደር፣ አርሶ አደር፣ ወጣት፣ ተማሪ፣ አስተማሪ፣ እናቶች፣ አባቶች፣ ጭቁን ወታደር፣ ሠራተኞች፣ ሴቶች፣ ታዳጊ ሕጻናት፣ ወዘተ። ይህን ኃይል ይዞ "ሕዝባዊ መንግሥት" የሕዝብን የሥልጣን የበላይነት መቀበል ነውና እንዴት ተደርጎ?

የ 1968 ዓ.ም. ሜይ ዴይ የኢሕአፓን ጥንካሬና የትግል ውጤት የተመለከቱ ደርጎች፣ መኢሶን፣ ወዝ ሊግ፣ ስለ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ከማሰብ ይልቅ ኢሕአፓን ማጥፊያ ጥይት ሚቀባበልበትን፣ መውጊያ ጩቤ የሚሳልበትን፣ ማነቂያ ገመድ የሚገመድበትን፣ አሳሽ ቡድን የሚሰማራበትን፣ ግድያ "በነጻ እርምጃ" የሚካሄድበትን፣ ግድያ በዘመቻ "ቀይ ሽብር" የሚፋፋምበትን ማጤንና ማውጠንጠን ጀመሩ፤ ለተግባራዊነቱም ቀጠሉ። የሥልጣን ጥማቸው ህልውና ቅድሚያው ከኢሕአፓ መጥፋት ጋር መሆኑን ተማምለው በገዳዩ መሪያቸው ፋሽስቱ መንግሥቱ ኃይለማርያም ሥር ተንበረከኩ። ይህ ነው ሀቁ።

ደርግ ከሥልጣን ማግሥቱ ጀምሮ ያካሄደውን አፈናና ግድያ በሠፊው ይቀጥልበት ዘንድ ደረጃ በደረጃ እቅድ ወጣለት፣ ዘመቻ መምሪያ ድረስ ተዘረጋለት። በሀገር አቀፍ ደረጃ መጋቢትና ሚያዝያ ወር 1969 ዓ.ም. በተካሄዱ የቤት ለቤት አሰሳ በርካታ የኢሕአፓ ልጆች ለእሥርና ለመስዋዕትነት ተዳረጉ። ከሰኔ 1969 ዓ.ም. ገደማ የጀመረው "ነፃ እርምጃ" በርካታዎችን በየመንገዱና አደባባዩ እየረሸነ ተጓዘ። በዚህ ሂደት የዛሬ 43 ዓመት ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ሜይ ዴይን አስታኮ በኢሕአፓ የተካሄደው የመጨረሻ ሰላማዊ ሰልፍ እጅግ በሚዘገንን መልኩ እልቂት አስከተለ። ተዘጋጅቶ ይጠባበቅ የነበረው የደርግ ወታደር ያለአንዳች ርህራሄ ሰልፈኛው ላይ የጥይት እሩምታ አርከፈከፉ። በየአካባቢው በርካታ ወጣቶች በየአስፋልቱ፣ በየጉራንጉሩ ተዘረሩ። ድንኳን ያልተተከለለት ልቅሶ፣ ቀብር ያልተኬደበት እየዬ፣ አባቶችን አንገት ያስደፋ ሀዘን፣ እናቶችን ያወራጨ ዱብ ዕዳ፣

ሕጻናትን ዝም ያሰኘ ሰቀቀን፣ በየመንደሩ ድል ተቀዳጀ። ፋሺዝም ደም በደም ተጎናጸፈ። የሕዝብን ልጅ ጨፍጭፎ "ሕዝባዊነት" ይህ ነው የደርግና ከባቢዎቹ ታሪክ።

በዚህ ያላበቃው የደርግ ጭፍጨፋ በ1970 ዓ.ም. ሀገር አቀፍ ሽብር፣ ቀይ ሽብር፣ ዘመቻ ግድያ በአብዮታዊና ዘመቻ መምሪያ ሥር በከተሞች ከታች ወለል ቀበሌ፣ በየገጠሩ ከወረዳ ጀምሮ በገዳይ ካድሬዎች በማዋቀር ሀገራችን በታሪኳ አይታ የማታውቀው እልቂትና ጭፍጨፋ በየቀኑ በትንሹ ለሁለት ዓመት እየዘገየም እስከ 1978 ዓ.ም. ድረስ አስተናግዳለች። በዚህ ሕዝባዊ እልቂት ዘር፣ ሃይማኖት ጾታ፣ ዕድሜና ሙያ ሳይለይ ኢሕአፓ እንዳደራጀው ጭፍጨፋውም በዚያው መጠን ተካሄደ። የ11 እና የ12 ዓመት ሕጻናት ሳይቀሩ ታሠሩ ተገደሉ፣ የሃይማኖት አባቶች ሳይቀሩ ተረሸኑ፣ የተገደሉ እናትና አባት የዘመኑን ጨካኝነት አበሰሩ፣ እርጉዞች ታሠሩ፣ ተረሸኑ ይህ ነው የደርግ፣ መኢሶንና ወዝ ሊግ ማንነት።

በዚህ ደም ላይ ኢማሌድኅ አብዐ፣ ኢሠፓአኮ ተመሥርቶ፣ ኢሠፓ ተወልዶ ሻለቃ/ኮነሌል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከወታደር ወደ ሲቪል ተቀይረው ኢሕድሪ ተመሠረተ ተብሎ ሲደገስ እውን ሀገር የ17 ዓመት የተውኔት መድረክ አልነበረችምን? የደርግ የግፍ አገዛዝ ዘመን ኢትዮጵያና ልጆቿን በልቶ ዛሬ ለደረስንበት አስከፊ የዘር ፖለቲካ ድልድይ የዘረጋ አይደለምን? በኢትዮጵያ ላይ ባነጣጠሩ ባዕዳን ኃይላትና በትግል ስም ሀገራቸውን በሸጡ የውስጥ አርበኞች የተሠራው ጣምራ ሤራ ጊዜና ትውልድ ገና ያወጣዋል።

<<ያ ትውልድ ተቋም>> የ1969 ዓ.ም. የሜይ ዴይ እልቂትን አስመልክቶ ያቀረብነው መልዕክት አሁንም ገዳይ መንግሥቱ ኃይለማርያምን እንደ ጀግና ለማውጣትና ለመካብ የሚደረጉ ሁኔታዎችን ለመከላከል የሰማዕታት ቃል ኪዳን አለብንና አቅርበናል። በግፍ በተጨፈጨፉ የሜይ ዴይ ሕጻናትና በቀይ ሽብር ሰማዕታት ማሾፉን ለተያያዛችሁ ግድያችሁ፣ ግርፊያችሁ፣ ዘረፋችሁ፣ አስገድዶ መድፈራችሁ፣ ሌላም ትዝ እያለ የሚያባንናችሁ የህሊና ቁስል ውጤት ነውና የምታደርጉትን አታውቁምና ይቅር ይበላችሁ።

የእኛ ልጆች በሞታቸው ስንኮራ እናንተ ትባንናላችሁ፣ እኛ ሙት ዓመታችንን ስንዘክር እናንተ ያባንናችኋል፣ እኛ ዳሮ ነጋሽን ስናነሳ እናንተ ትሳቀቃላችሁ፣ እኛ ሜይ ዴይ ስንል እናንተ ትደበቃላችሁ፣ እኛ ቀይ ሽብር ስንል እናንተ በሽብር ትዋጣላችሁ፣ እኛ ኢሕአፓ ስንል የልብ ትርታችሁ ይጨምራል። ቢገባችሁ ግና ታሪክን በታሪክነቱ እያነቃችሁም ቢሆን መቀበል በሳልነት ነው። ጥንት እንዳልነው አሁንም ሀቅ አንቋችኋል፤ ዛሬም ይተናነቃችኋል። እኛ የደርግን ጥፋት ስንዘከዝክ እንደ ጲላጦስ እጃችንን ታጥበን አይደለም። ጥፋታችንን አምነን ተምረን የምናስተምር ነን። ግልጽ ማድረግ የምንፈልገው ግና የሜይ ዴይም ሆነ የቀይ ሽብር ሰማዕታት ከሕዝብ ወገን ተሰልፈው ለሕዝባችንና ለሀገራችን ሲሉ ሕይወትን የለገሱ ናቸውና ዛሬም ነገም እንዘክራቸዋለን፤ እናከብራቸዋለን።

«ያ ትውልድ ተቋም» ለሀገራቸው ክብርና ለሕዝባቸው መብት ሲፋለሙ ክቡር ሕይወታቸውን ለሰዉት የኢትዮጵያ ጀግኖችና የያ ትውልድ ሰማዕታት መታሰቢያነት በያ ትውልድ ስም ያ ትውልድ ድረ ገጽን (www.yatewlid.com www.yatewlid.org ) ለሕዝብ ይፋ ያደረግንበትን ሚያዝያ 23 ቀን 2004 ዓ.ም. ስምንተኛ ዓመት ስናከብር ታሪካችን ከትውልድ ትውልድ ይተላለፍ ዘንድ በሩን ከፍተናልና በታላቅ ደስታ ነው። ዛሬ አጠገባችን የሌሉትን ወንድምና እህቶቻችንን ቢያንስ ስማቸውንና ምስላቸውን እንደያዘ ሚተላለፍ፣ በየትም ሀገርና ቦታ ሆነው የሚያዩት ሐውልት

**አቁመንላቸዋልና ከተቀበልነው ኑዛዜ ጠብታዋን በማድረጋችን፡ በመጀመራችን እየተደሰትን ከፊታችን የተደቀነውን ከባድ ኃላፊነት በትጋትና በሙሉ ስሜት ለመወጣት ቃል በመግባት ነው።**

**ክብር ለሜይ ዴይ** 1969 **ዓ.ም**. **እና ለቀይ ሽብር ሰማዕታት**!!!

**ዛሬም ስለ ፍትህ እንጮኻለን**!

*«**ያ ትውልድ ተቋም**» **ለመረጃ ምንጭነት**!*
*__**የተጐዱ ወገኖችን ለመርዳት**__!*
*__**ለያ ትውልድ መታሰቢያነት**__!*

**«ያ ትውልድ ተቋም»**




- **ስልክ** ፡ (703) 300 4302
- **ኢሜል** : yatewlid@gmail.com,
- **ድረ ገጽ** : http://www.yatewlid.com, http://www.yatewlid.org, www.redterror.org, www.thatgeneration.org
- **ምስለ ገጽ** : yatewlid

***ሚያዝያ*** 21 **ቀን** 2012 **ዓ.ም**. (May Day 2020)

***<u>ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም.ን አስመልክቶ በየዓመቱ በ "ያ ትውልድ ተቋም" ከወጡ ጽሑፎች</u>***

http://yatewlid.com/images/PDF/YT/YT_Issue/YTT-May-Day-2013.pdf
http://yatewlid.com/images/PDF/YT/YT_Issue/YT_Vol_1/Ya_Tewlid_Vol_1_No_5_Miazia_21_2006.pdf
http://yatewlid.com/images/PDF/YT/YT_Issue/YT_Vol_3/Ya_Tewlid_Vol_3_No_5_Miazia_21_2008.pdf
http://yatewlid.com/images/PDF/YT/YT_Issue/YT_Vol_5/Ya_Tewlid_Vol_5_No_4_MayDay_2010.pdf
http://yatewlid.com/images/PDF/YT/YT_Issue/YT_Vol_6/Ya_tewlid_Vol_6_No_3_MayDay_2011.pdf